" ፩ ሁኑ! "

# የአማራ ማኅበር በኔዘርላንድ

# ሕገ-ደንብ

# Vereniging van Amharas in Nederland (VAN)

# Amhara association in Netherlands

# Bylaw

*29 June 2024*

*Amsterdam, Netherland*

## መቅድም

የአማራ ማሕበር በኔዘርላንድ የኔዘርላንድ አገረ-መንግሥትን ሕግና ደንብ ጠብቆ በማሕበሩ አባላት ፍቃደኝነት እና ስምምነት በይፋ የተቋቋመ ሕዝባዊ ማሕበር (Civic Association) ነው። በተለያዩ ምክንያቶች ከአገር ቤት ለቀው እንዲሁም በኔዘርላንድ ተወልደው የሚኖሩ የአማራው ማሕበረሰብ በሚኖሩበት የኔዘርላንድ አገር ውስጥ ጠቃሚ ባህላቸውን እና ልምዶቻቸውን በፆታ፣ በዕምነት፣ በዕድሜ እና በፖለቲካ አመለካከት ላይ ልዩነት ሳያደርጉ በወንድምማማችነት እና በእህትማማችነት መንፈስ ተሰባስበው ሳይለያዩ እርስ በርስ በመተሳሰብ የጋራ አቅማቸውን በማጎልበት ለመረዳዳት፣ በማንነትን ባህልን፣ የግል እና የገራ አቅምና ክህሎቶችን ለማዳበር ታስቦ የተመሠረተ ነው።

የአማራ ሕዝብ የረጅም ዘመን ታሪክና ሥልጣኔ ያለው ታላቅ ነገድ፤ ለረጅም ዘመን የቅርብና የሩቅ ተስፋፊና ወራሪ ሃይሎችን በመቋቋም በከፈለው የደምና የአጥንት መስዋዕትነት ኢትዮጵያን የገነባ ሕዝብ፤ በኢትዮጵያ ምድር ሀገሪቱን ሀገሬ ሕዝብኑም ህዝቤ ብሎ ተጋብቶ ተዋልዶ ለዘመናት የኖረ ሕዝብ፤ ብሄራዊ እሴቶችን ተላብሶ ፣ በፈጣሪው የሚመካ ፣ጨዋ፣ ኩሩ ሕዝብ ሆኖ እስካሁን ቆይቷል። ከዛም አልፎ የአማራ ህዝብ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድነት ነጻነትና እኩልነት የላቀ መስዋዕትነት ሲከፍል የኖረ ቢሆንም ከ20ኛዉ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ወዲህ አገር በቀል ፀረ አማራ ድርጅቶች እና ፀረ አማራ ስርዓት አስፈፃሚዎች በአማራው ነገድ፣ በአማራ ወዳጆች እንዲሁም አማራዊ፡ እሴቶች ፣ባህሎች እና እምነቶች በሚያንጸባርቁ ወዳጆች ላይ የሀሰት ትርክትን ተመርኩዘው የዘር ማፅዳት እና የዘር ማጥፋት ወንጀል ፈፀመዋል እየፈፀሙም ነው። የኢትዮጵያ መንግስትም የተበዳዮች ድምፅ እንዳይሰማ በሀገሪቱ ባሉ ሚዲያዎች እንዳይዘገብ አድርጓል፣ ፍትህ እንዳይሰጥ ሆን ብሎ ድርጊቱን እና ሚኞችን በመካድ ለወንጀሉ ተባባሪ መሆኑን እያረጋገጠ ነው። ለዚህ ሁሉ ግፍ ሀይ ባይ መጥፋት አንደኛው ምክንያት ጉዳዩን ተከታትሎ ለአለም አቀፍ ማህበር የሚያሳዉቅ የተጠናከረ አማራ መር አደረጃጀት ባለመኖሩ ስለሆነ በኔዘርላንድ ሀገር የምንገኝ አማራዎች እና አማራ ወዳጆች የተጠናከርን የወገኖቻችን ድምጽ ለመሆን እንንድንችል ይህንን ማህበር አቋቁመናል።

የወገኖቻችን ድምጽ ለመሆን ከሚደረጉ ጥረቶች ባለፈ በአማራው ህብረተሰብ ላይ የተፈፀመን የዘር ማጽዳት እና የዘር ማጥፋት ዘመቻ እንዲቆም የድርሻችንን ለመወጣት፣ በሁሉም የልማት እና መልሶ ማቋቋም መስከ ድጋፍ ለማድረግ፣ በአገር ቤት በጦርነት ምክንያት የተጎዱ ወገኖችን ለመደገፍ እና ለምንኖርበት ለኔዘርላንድ መንግስትም ሆነ ለዓለም አቀፍ ሰላም ወዳድ መንግስታት ሁሉ ባለማቋረጥ በተቀናጀ መልኩ የወገኖቻንች ጉዳት ለማጋለጥ ሁለተናዊ አቅማቸን እና ኃይላችን በማስተብር በጋራ ተደራጅቶ መሥራት ይኖርብናል። እነዚህ አላማዎቻችን ግብ እንዲደርሱ አማራውን እና ደጋፊ የህብረተሰብ ክፍሎችን ግልፅነት እና ተጠያቂነት ባለው አሰራር በማደራጀት በአንድነት ለመስራት የሚያስችል ማህበር፣ ህገደንብ እና የአሰራር ማእቀፍ መኖር እናዳለበት አጠያያቂ አይደለም። ይህን ለማሳካት በኔዘርላንድ እና በሌሎችም ሀገራት ከሚገኙ አማራ መር ማህበራት ህገደንቦች መሰረት በማድረግ፣ ለኔዘላንድ ማህበር የሚጠቅሙ የስራ ክፍሎች እና አንቀጾችን በመጨመር እና በማሻሻል ማኅበሩ ለሌሎችም አቻ ማህበራት ተሞክሮ እንዲሆን ይህ የአማራ ማኅበር በኔዘርላንድ መተዳደሪያ ሕገደንብ ተዘጋጅቷል።

# 1 ትርጓሜ ፣ ዓላማ ፣ ተግባራት እና መርሆች

## 1.1 መጠሪያ እና ትርጉም

1.1.1 የማሕበሩ የአማርኛ መጠሪያ በዋናነት ተገቢነት ያለው ስያሜ “ የአማራ ማሕበር በኔዘርላንድ” ሲሆን ምህፃረ ቃሉም አማኔ ይሆናል። ማሕበረሰባችን እንደ አካባቢው አስተዳደግ በተለያየ ፊደላት ስለሚጠቀም አማራ፣ ዓማራ፣ ዓምሓራ፣ ዓምሐራ፣ አማራ፣ አምሐራ፣ ዐምሓራ፣ ዐማራ፣ ዐምሐራ፣ አምሃራ፣ ዓምሃራ፣ አምሀራ ፣ዓምሀራ የሚለውን ቢጠቀሙ ተገቢነት አለው። ይህ አጠቃቀማቸው ጠቀሜታው በአባሎቻችንም ሆነ ደጋፊዎቻችን በፅሁፉ የሕግ ጉዳዮች ቢከሰቱ አግባብነት እንዲኖረው ነው። የማሕበሩ የኒዘርላንድ ቋንቋ መጠሪያ ስያሜ “Vereniging Van Amharas in De Nederland” (VAN) ነው። በእንግሊዘኛው ‘’Amharas Association in the Netherlands”(AAN) ተብሎ ይጠራል::

1.1.2 የማኅበሩ አርማ እና ትርጓሜው በአባላቱ ምርጫ መሰረት ተድርጎ በቀጣይ ይፃፋል።

1.1.3 በዚህ ሰነድ በወንድ የተገለፀው ለሴትም ይሆናል።

1.1.4 የአማራው ማህበረሰብ ማለት በኔዘርላንድ የሚኖሩ የአማራ ነገድ እና በአማራው ነገድ ላይ የተፈፀመውን ጀኖሳይድ የሚያምኑ እና አማራው በማንነቱ ተደራጅቶ የሚያደርገውን የፍትህ እና ህልውና ማዳን ትግልን የሚደግፉ ሌሎች ኢትዮጵያውያንም ለማለት ነው።

1.1.5 የማኅበር አባል ማለት በኔዘርላንድ የሚኖር የማኅበሩን አባልነት መስፈርት በደንቡ መሰረት ያሟላና በፈቃዱ የአባልነት ቅፅ ሞልቶ ማኅበሩን የተቀላቀለ ማለት ነው።

1.1.6 ደጋፊ (ደጋፊ አባል) ማለት የማኅበሩን አባልነት መስፈርት የማያሟሉ ነገር ግን ለአማራ ማኅበር ቀና አመለካከት ያላቸው እና የሚደግፉ አካላት ማለት ነው።

1.1.7 ጠቅላላ ጉባዔ ማለት የማኅበሩ አባላት በሙሉ የሚሳተፉበት ጠቅላላ ስብሰብ ማለት ነው።

1.1.8 አማካሪና ሽምጋይ ቦርድ ማለት ማኅበሩ ውጤታማ እንዲሁን ለሚፈጠሩ ማናቸውም ችግሮች ልዩነቶች የሚሸመግል የሚመክር ማለት ነው።

1.1.9 ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ማለት በጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጡ የማኅበሩ የሥራ አስፈፃሚ አካላት ናቸው።

1.1.10 የስራ ክፍሎች ወይም ኮሚቴዎች ማለት የማኅበሩን ተግባራት የያዙ የስራ መደቦች ለማለት ነው።

1.1.11 አጋር ተቋማት ማለት ለአማራ ሕዝብ ማንነት እና ሰባዊ መብቱ መጠበቅ ቀና እና ጤናማ አመለካከት ያላቸው ሆኖ በተመሳሳይ መንገድ የተድራጁ ተቋማት ማለት ናቸው።

**1.1.12** አስመራጭ ኮምቴ ሲባል በጉባዔው የተመረጡትን አምስት አባላት የያዘ ስብስብ ሲሆን ጉባዔው ወይም ምክርቤቱ በሚያዝዘው የአስመራጭነት ተልኮ የሚወጣ ማለት ነው።

## 1.2 ራዕይ ፡

በኔዘርላንድ የሚገኙ ሁሉም የአማራ እና አማራ ወዳድ ወገኖችን በአንድ ጥላ ስር ተሳባስበው እና የእርስ በርስ ግንኙነታቸው ዳብሮ አማራውንም ሆነ ኢትዮጵያን በሁሉም ዘርፍ ሲታደጉ ማየት።

## 1.3 ዋና ግብ፡

የማኅበሩን አባላት እና ደጋፊዎች በማሳደግ እና የማህበራዊ ግንኙነታቸውን በማጠናከር የአማራውን የህልውና ማዳንና ፍትህ ማስፈን ትግል በቀዳሚነት በመደገፍ አማራው በኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ልማት ፍትሀዊ ተጠቃሚ እንዲሆን እና መልሶ እንዲቋቋም በአንድነት ተሳትፎ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ እንዲደረግ ማስቻል።

## 1.4 ዓላማ፡-

1.4.1 በቀዳሚነት በኔዘርላንድ አገር ተበታትኖ የሚኖሩ የአማራው ማሕበረሰብን በመተሳሰብ እና በመከባበር ላይ መሠረት ባደረገ የመቀራረብ ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖር በጋራ የምንመራበት ስርዓት በማዘጋጀት ተሻጋሪ ጠንካራ ማኅበር መፍጠር።

1.4.2 የጋራ አመራርን ፣ግልፅነትን፣ ታማኝነትን እና የስራ ክፍፍል ስርዓት በመፍጠር አማራውን ፍላጎት የሚያሟላ ሁለተናዊ የድጋፍ አቅምን በቀጣይነት ለማሳደግ

1.4.3 በተመሳሳይ መንፈስ በአውሮፓና በሌሎች አህጉራት ከሚኖሩ የአማራው መሠል ስብስቦች ጋር በእህትማማችነትና በወንድማማችነት መንፈስ የተቃኘ ስርዓት ባለው መንገድ ግንኙነትን አጠናክሮ ጠንካራ የአማራ ህብረትን ለመፍጠር።

1.4.4 ካለፉት 50 ዓመታት ጀምሮ በአማራ ሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን የዘር ፍጅትና የሰብአዊ መብት ጥሰት ለዓለምአቀፉ ማህበረሰብ ለማጋለጥ።

1.4.5 የአማራ ሕዝብ ለሚያደርገዉ ሁለገብ የህልውና ትግል፣ አስፈላጊውን የሞራል፤ የገንዘብና ቁሳቁስ እንዲሁም የዲፕሎማሲ ድጋፍ ማድረግ።

1.4.6 የአማራን ሕዝብ ታሪክ፣ ቋንቋ፣ ባህል፣ ቅርስና ትውፊት ለዉጭዉ ማህበረሰብ ለማስተማር፣ ለማስተዋቅ እና ለመጠበቅ።

1.4.7 በኔዘርላንድ የሚኖሩ አማሮችን እና ደጋፊ ኢትዮጵያውያንን ለሕልውና ትግሉ በአንድነት እንዲቆሙ እና እንዲደግፉ ለማስተባበርና ለማደራጀት።

1.4.8 በኔዘርላንድ የተወለዱ ወይም የመጡ ህፃናትን እና ወጣቶችን የአማራውን ፣የኢትዮጵያን እና የኔዘርላንድን ባህል ቋንቋ የመሳሰሉትን እንዲያውቅ ለመደገፍ

1.4.9 በኔዘርላንድ ከሚኖሩ የአማራ ባለህብቶችና ድርጅቶች፣ ከሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ድጋፍ እንዲሰጡ ለመስራት ።

1.4.10 የአማራ ሕዝብ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና ፓለቲካዊ ተሳትፎና ተገቢው ውክልና እንዲኖረው፤ እኩልና ፍትሀዊ ተጠቃሚ እንዲሆን መስራት።

1.4.11 የአማራን ሕዝብ ጥቅም ለማስጠበቅ በመላዉ ዓለም ከሚገኙ የአማራ አደረጃጀትና ማህበራት ጋር በጋራና በትብብር መስራት።

## 1.5 የጽህፈት ቤት አድራሻ

1.5.1 የማኅበሩ ዋና ጽ/ቤት አምስተርዳም ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች ከተሞችም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሊያቋቁም ይችላል።

1.5.2 የማኅበሩ ጽ/ቤት የሚያስተዳድረዉ የራሱ ድረ ገጽ (ዌብ ሳይት)፤ ኢሜይል፤ ቲውተር፣ የፓስታ አድራሻ ፣ስልክ እና ሌሎች ለማኅበሩ ጠቂሚ ሚዲያዎች ይኖረዋል። በሚከፈቱበት ወቅት ስያሚያቸው አማርኛን እና እንደአስፈላጊነቱ ኔዘርላንድ እንግሊዘኛን እና ወይም ሌላ ቋንቋ ማካተት ይችላል።

## 1.6 የማሕበሩ አጠቃላይ የአሰራር መርሆዎች

1.6.1 የሥራ ክፍፍል መፍጠር፣ የክትትልና የቁጥጥር ስልቶችን መዘርጋት፤ በግልጽነኝነትና ተጠያቂነት መርሆች ላይ የተመሠረተ የአሰራር ስርዓት መተግበር፤

1.6.2 የማኅበሩን አባላትና የአመራር አካላት መብትና ግዴታቸዉን ጠንቅቀዉ በማወቅና የድርጅቱን መተዳደሪያ ደንብ በማክበር በድርጅቱ ዉስጥ የሕግ የበላይነትን ማስፈን፤

1.6.3 ማኅበሩ የሲቪክ ማኅበር እንደመሆኑ መጠን አባላትን ለማምጣት እና በአንድነት ለመጠናከር ያግዝ ዘንድ አባሉ የፖለቲካ አይዶሎጂ እና የእምነት ልዩነቶችን በማክበር በጋራ ጉዳዮች ላይ አተኩሮ መሰራት ይኖርበታል። የማኅበሩን ደንብ ሳይጥስ ሐሳብን በነፃነት የመግለጽና የማንሸራሸር መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ለብዙኃን ውሳኔ ተገዥ መሆን ይገባል፤

1.6.4 የተናጠልን የስራ ስምሪት መፈፀም እንደተጠበቀ ሁኖ የቡድን የመደጋገፍ ስራዎችን ሁሉም አምኖ መቀበል እና መተግበር ይኖርበታል፡፡

1.6.5 የማኅበሩን መዋቅር ጠብቀዉ የሚተላለፉ የበላይ አካላት ውሳኔዎቹንና መመሪያዎችን ማክበርና ተግባራዊ ማድረግ፤

1.6.6 ሥርዓትና ደንብን ያልተከተለ አሰራርን፣ የግለሰብ ፈላጭ ቆራጭነትንና አፍራሽ ቡድንተኝነትን ለማስወገድ በጋራ ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ መመራራት ይገባል፤

1.6.7 በማኅበሩ በሚደረጉ የአመራር ቦታ ምርጫዎች የፆታ ተዋፅዖን በሚያበረታታ ይሰራል፡፡

1.6.8 ጠቅላላ የአባላት ጉባዔ የማነኛውም የስራ ክፍል ወይም አደረጃጀት የተሰጠውን ስራ በአማካሪ ቦርዱ አስተያየት መነሻ ወይም ጉባዔው በራሱ መንገድ ገምግሞ ውጤታማ ስራ መስራቱ ከታመነበት በአዲስ ለመተካት ተጨማሪ ወጭ እና ጊዜ ማጥፋት ስለማያስፈልግ ተጨማሪ ጊዚያት ይሰጣል፡፡ በአንፃሩ ሀላፊነቱን ያልተወጣን ገምግሞ የጊዜ ገደቡን ሳይጠብቅ ሊበትን እና በአዲስ እንዲተካ ማድረግ ይችላል፡፡ በአዲስ ሲተኩ ለርክክብ እስከ ሶስት ወር ተጨማሪ ይሰጣል፡፡

1.6.9 የማኅበሩ አመራርም ሆነ አባል ለማኅበሩ ስራዎች ሲሰራ ለማኅበሩ ለሚያስፈልጉ ወጭዎች እና ለማኅበሩ ተግባራት ግለሰቦች ከግላቸው በገንዘብ(የእውቀትን እና ሌሎችን አይጨምርም) ለሚያወጡት ወጭዎች መሸፈኛ የሚሆን የስራማስኬጃ በጀት ይኖረዋል፡፡ በጀቱን ለመወሰን ዝርዝር ተግባራትን እና የሚያስፈልገውን ገንዘብ በክፍሉ አዘጋጅቶ ስራ አስፈፃሚው ሲያምንበት በምክርቤቱ አፀድቆ ለኦዲት በሚያመች አሰራር መጠቀም ይችላል፡፡

1.6.10 የማኅበሩ አባላትን እና ደጋፊ የመልክት መለዋጫ ዋትስአፕ እና መሰል ግሩፖችን የስራ አስፈፃሚው ሰብሳቢ፣ምክትል ሰብሳቢ ፣ፀሀፊ እና መረጃ ክፍል ሀላፊው ወይም ከክፍሉ በክፍሉ ሰራተኞች የተወከለ ብቻ በበላይነት ይቆጣጠሩታል፡፡ ሌላም አስፈላጊ ምክንያቶች ካጋጠሙ አስፈፃሚ ኮሚቴው በጋራ ወስኖ ከኮምቴው አባል ተጨማሪ መወከል ይችላል፡፡

1.6.11 ማኅበሩ በህዝባችን በታመነባቸው በዓላት ላይ ለምሳሌ የአድዋ ድል ቀን፣ የአርበኞች ቀን፣ የካራማራ ድል ፣ የአሸንድየ የመሳሰሉትን በዓላት የኢትዮጵያን አንድነት ታላቅነት ክብር በሚመጥን የአገር ባለውለታ አባት እናቶቻችንን አስተዋፅኦ በሚዘክር ማክበር ይኖርበታል፡፡ ሌሎች አቻ ማህበራት ጋርም አብሮ ያከብራል፡፡ ማኅበሩ በሌሎች ተግባራት ከሌሎች የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ነገዶች ማኅበር ጋር በጋራ አቅዶ ተስማምቶ መስራት የሚገባው የአማራ ማንነት መኖሩን እና በማንነቱ መደራጀቱን እንዲሁም መንግስት መር ጀኖሳይድ በአማራ ላይ በመፈፀሙ ፍትህ እንደሚያስፈልግ ማህበራት ካመኑና የአማራ ማኅበር አስፈፃሚው ኮሚቴ ሲወስኑ ብቻ ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሁኖ በማኅበሩ ተነሳሽነትና መሪነት ለማኅበሩ የሚጠቅሙ ተግባራት ሲኖሩ አባላትን እና ህዝባችንን ቅሬታ የማያስነሳ የማይከፋፍል ፣ ደንቡን የማይጥስ መሆኑ በአስፈፃሚው እና ምክርቤቱ ተገምግሞ ሲታመንበት መስራት ይቻላል፡፡

1.6.12 የማኅበሩ አባላት እና አመራሩ ያለስጋት እና ጥርጣሬ በማኅበሩ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ እንዲሁም አዲስ አባላትም እንዲቀላቀሉ ለማነኛውም የማኅበሩ አስተዳደር መዋቅሮች ወይም የስራ ክፍሎች ለሚመረጥ አካል የተሻለ የስራ አፈፃፀም ያለውን በመሪነት የሚያስቀምጥ ዲሞክራይሲያዊ የመረጣ ስርዓት በማውጣት ይተገበራል፡፡

1.6.13 በማነኛውም የአማራ ማኅበር መዋቅር ማለትም አባል፣ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አመራር እና አባል፣ የኦዲት እና ቁጥጥር ኮሚቴ ፣ የስነምግባር እና ሕግ ክፍል ፣አማካሪና ሽምጋይ ቦርድ እንዲሁም ሌላ የአስተዳደራዊ መዋቅር በሚፈጠር መደብ የሚወከል ወይም የሚመረጥ አመራር ከማኅበሩ አባል ይመረጣል፡፡

1.6.14 የአባልነት ቅፁን ያልሞላ በማኅበሩ የአባላት ጉዳዮች ላይ ሀላፊነት መውሰድም ሆነ በውሳኔ ስብሰባዎች መሳተፍ እና መወሰን አይችልም፡፡

1.6.15 የማኅበሩ ዋና አደረጃጀቶች ማለትም ጠቅላላ ጉባዔው እና አስፈፃሚው ያለመጓተት ፈጣን ውሳኔ እየሰጡ ሊሰሩ ሲገባ ሳይሆን ሲቀር ቢያንስ አንድ ጊዜ ጥሪ ተደርጎ ሳይፈፀም ቢዘገይ ወይም ቢቀር ደረጃውን ጠብቆ በአማራጮች እያስወሰነ ወይም እየወሰነ ይተገብራል፡፡ ለምሳሌ አስፈፃሚው ጠቅላላ ጉባዔ ጠርቶ ሳይሟላ ቢቀር ( ከ50%+1በታች ቢሆን)የስራ አስፈፃሚው ደንቡን ባልጣሰ በራሱ ወስኖ ይተገብራል፡፡ ከላይ ወደታች ባለው አሰራርም እንዲሁ ይሆናል፡፡

1.6.16 የማኅበሩን ተግባራት እና አባላትን ቁጥርን መሰረት ተደርጎ የስራክፍል አመራርን ወይም ኦፊሰርን አስፈፃሚው እና ንኡስ ኮሚቴዎችን መጨመር ወይም ቀንሶ በውክልና ማሰራት ይቻላል፡፡

1.6.17 ማነኛውም የስራ ክፍል ወይም ኮምቴ ይህን ሕገደንብ መነሻ አድርጎ ደንቡን በማይፃረር እና የሌሎችን የስራ ክፍል ስልጣን ወይም ተግባር በማይጋፋ የራሱን ተግባር ዉጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉትን የውስጥ ዲስፐሊን፣ እቅዶችን፣ ተግባራትን እና ሌሎችም በጋራ ውሳኔ እያፀደቀ ማዘጋጀት እና መስራት ይችላል።

1.6.18 ማነኛውም አመራር ወይም የኮሚቴ አባል ሲቀየር ወይም ሲለቅ አስፈላጊውን መረጃ ዶክመንት ለተተኪው ወይም ለታዘዘው ማስረከብ ይኖርበታል። የማኅበሩ መዋቅር ጀማሪ እና በመጠናከር ላይ ያለ ከሆነ ጠቅላላ ጉባዔው አስፈፃሚ ኮምቴውን ቅድሚያ መርጦ ከሌላ አደረጃጀት ወይም ኮሚቴ ጋር በመተጋገዝ ምክርቤቱ እንዲቋቋም ያስተባብራል ይደግፋል እስከዛውም ይሰራል።

1.6.19 ማነኛውም አመራር አማራንም ሆነ ማኅበሩን የሚጎዱ ውሳኔዎችን ሚስጥሮችን በጥንቃቄ በመያዝ እና በመታመን አርያ መሆን ይጠበቅበታል። ይህን ሳያደርግ የተገኘ የሚሰጠውን ውሳኔ ለመቀበል ዝግጁ እና ፍቃደኛ ሊሆን ይገባል። በማነኛህም የስራ ክፍል አመራር ማዕከላዊነትን ሳይጠብቅ ሳያስፈቅድ ማኅበሩን የሚጎዳ አመራሩን ጥርጣሬ የሚከት እና የሚከፋፍል የጎንዮሽ ስብሰባም ሆነ በማይመለከተው የስራ ክፍል ስምሪት መስጠት አይገባም። ነገር ግን በራሱ የስራ ክፍል ስራውን ለመስራት አመራሮች ፍቃደኛ ከሆኑ እና ሕገደንቡን የሚፃረር ስራ እስካልሰራ በራሱ ተነሳሽነት ሰብስቦ መወያየት ይችላል።

1.6.20 የአማራ ሕዝብ እና የሌላ ማነኛውም አካል በልዩልዩ ቦታዎች ማለትም ሚዲያ፣ መድረክ፣ ስብሰባ፣ በግል ውይይቶች፣ በመሳሰሉት ልዩልዩ ጉዳዮች ቢያጋጥሙት በአማራው ላይ የተፈፀመን የዘር ማጥፋት ፣ የዘር ማፅዳት እንዲሁም የአማራውን የህልውና ትግልን የካደ አባልም ሆነ ደጋፊ ተጨባጭነቱ ከተረጋገጠ ( እንደ አስፈላጊነቱ ቢያንስ አንዴ ተመክሮ ያላስተካከለ) በአባልነት ሊቀጥል አይገባውም። ውሳኔ ተግባራዊ የሚደረገው በስራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ይሆናል። ጥፋተኛው ቅሬታ ካለው ለምክርቤቱ ወይም ጠቅላላ ጉባዔ ማቅረብ ይችላል።

1.6.21 የማኅበሩ ሕገደንብ ለማኅበሩ እድገት እና ጥንካሬ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እና ሁለት ሶስተኛው አባላት ሲያምኑበት ሕገደንቡ እየተሻሻለ የሚዳብር ይሆናል።

## 1.7 የማኅበሩ ተግባርና ተልዕኮ

1.7.1 በኔዘርላንድ የሚገኙ አማራዎች የሚገናኙባቸዉ እና የሚቀራረቡባቸው ማህበራዊ መድረኮችን መፍጠር።

1.7.2 ከመንግስታዊ አካላት፤ ከሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጀቶችና ከመገናኛ ብዙሃን ጋር ግንኙነት በመፍጠር በአማራ ሕዝብ ላይ የሚካሄደዉን የዘር ፍጅት ወንጀል በማጋለጥ፤ ድጋፍና ትብብር መጠየቅ።

1.7.3 በኔዘርላንድ ያሉ አማሮች ማኅበሩን እንዲቀላቀሉ እና እንዲያጠናክሩ እንዲሁም ለሁለንተናዊ ድጋፍ ግንባር ቀደም እንዲሆኑ መደገፍ።

1.7.4 በኔዘርላንድ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን አማራው ህልውናውን ታድጎ ኢትዮጵያን ለማዳን ከሚያደርገው ትግል ጎን እንዲቆሙ መቀስቀስና በደጋፊ እና በአባልነት ማኅበሩን እንዲደግፉ እንዲያጠናክሩ ምቹ ሁኔታ መፍጠር መደገፍ።

1.7.5 ሕዝባዊ ስብስባዎችን፤ ሰላማዊ ሰልፎችንና የሻማ ማብራት ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ድምጽ መሆን።

1.7.6 ወቅታዊ መግለጫዎችን በማዉጣት ለዓለምአቀፉ ማህበረሰብ መረጃ ማቅረብ።

1.7.7 በአማራው ነገድ ላይ የሚፈጸሙ የዘር ፍጅት፤ የዘር ማጽዳት፣ የጦር ወንጀሎችና የሰብአዊ ጥሰቶችን በሚመለከት ማስረጃዎችን በማሰባሰብ ሰነድ በማዘጋጀት የዲፕሎማሲ እና አድቮኬሲ ስራ መስራት።

1.7.8 በአማራ ሕዝብ ታሪክ፤ ቋንቋና ባህል ላይ ጥልቅ ጥናትና ምርምር እንዲካሄድ ማድረግ እንዲሁም ትምህርታዊ ሴሚናሮችና ሲምፖዚየሞችን ማዘጋጀት።

# 2 አንቀጽ 2 ፦ ስለ ደጋፊነት፣ አባልነት እና አመራርነት

## 2.1 ለአባልነት፣ ደጋፊነት ቅድመ ሁኔታዎች

2.1.1 ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ፣ የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ የተቀበለ ነገደ አማራ የሆነ ሁሉ የማኅበሩ አባል ወይም ደጋፊ መሆን ይችላል።

2.1.2 በአማራው ነገድ እና ማንነት መኖሩን የሚያምኑ፣ የአማራ ሕዝብ፡ ለሕልውናው፣ ለደህነነቱና ለነጻነቱ የሚያደርገውን ትግል ለመደገፍ ፈቃደኛ የሆኑ፣ በአማራው ላይ መንግስት መር የዘር ማፅዳት እና ዘር ማጥፋት መፈፀሙን ያመኑ፣ የአማራን ጥቅም እና መብት ከሚፃረሩ ማነኛውም የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ መንግስታዊም ይሁን መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወይም ቡድኖች አባል እና ደጋፊ ያልሆኑ፣ በኢትዮጵያን አንድነት የሚያምኑ እና የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ የተቀበለ ማንኛዉም ሰው የማኅበሩ ደጋፊ አባል መሆን ይችላል። ደጋፊ ለመሆን በአስፈፃሚው የተዘጋጀን ቅፅ መሙላት ይጠበቅበታል።

2.1.3 ከወንጀል ነፃ ያልሆነ፣ በሕግ በተከለከለ አደገኛ ሱስና መጥፎ ልማድ ውስጥ ያለ ማነኛውም ሰው የማኅበሩ አባል ወይም ደጋፊ መሆን አይችልም፡፡

2.1.4 የማኅበሩ ደጋፊ ማኅበሩን ደንብ በማይጥስ ማኅበሩን በእዉቀቱ፤ በገንዘቡና በሌላም በሚችለዉ መንገድ ለመርዳት ከፈለገ መርዳት ይችላል።

2.1.5 የማኅበሩ አባልም ሆነ የማኅበሩ ደጋፊ ጠቅላላ ጉባዔ፣ ምክርቤት ፣የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚያወጣውን መመሪያና ውሳኔዎችን ይፈፅማል።

2.1.6 ማነኛውም የማኅበሩ አባል ወይም ደጋፊ ጥርጣሬ የሚከት እና የሚከፋፍል የኅንዮሽ ስብሰባም ሆነ በማይመለከተው የስራ ክፍል ስምሪት መስጠት አይገባም። ማኅበሩን የሚጎዱ ውሳኔዎችን ሚስጥሮችን በጥንቃቄ በመያዝ እና በመታመን አርያ መሆን ይጠበቅበታል። ይህን ሳያደርግ የተገኘ የሚሰጠውን ውሳኔ ለመቀበል ዝግጁ እና ፍቃደኛ ሊሆን ይገባል።

## 2.2 የአባልነት መብት እና የደጋፊነት መብት

2.2.1 የማኅበሩ አባል የመምረጥ፣ የመመረጥ፣ውሳኔዎችን የመተቸት የማፅደቅ እና የመሻር ድምፅ የመስጠት መብት ይኖረዋል። ማነኛውም የማኅበሩ ደጋፊ የማኅበሩን አመራር የማወቅ እና ለምክክር እንዲጋበዙ የመጠየቅ መብት አለው።

2.2.2 አባላት የማኅበሩን የስራ አፈፃፀም የመተቸት እና ውሳኔዎችን የመወሰን ሙሉ መብት ያላቸው ሲሆን ደጋፊዎች ግን የመተቸት መብት እንጅ መወሰን አይችሉም። ማነኛውም የማኅበሩ ደጋፊ ለማኅበሩ አመራር መሟላት እና መጠናከር በግልም ሆነ በቡድን ፣በፅሁፍም ሆነ በተዘጋጀላቸው ወይም ባዘጋጁት መድረክ አስተያየት መስጠት ይችላሉ።

2.2.3 ማኅበሩ ለአባላት በሚያዘጋጀዉና አግባብ ባለዉ መገናኛ መድረክ በመሳተፍ ሐሳብ የማቅረብ፤ የመከራከር፣ መተቸት እና የመወሰን መብት አላቸዉ፤ ደጋፊዎችም እንዲሁ በተዘጋጀላቸው የውይይት ወይም በሌላ መገናኛዎች የመተቸት መብት አላቸው ።

2.2.4 የአባላትን የገንዘብ ወጭ በማይነኩ ወይም በማይጋሩ ወይም ለአባላት ብቻ ከሚመለከቱ ተግባራት ውጭ ባሉ በጋራ ጉዳዮች ላይ ለምሳሌ ሰልፍ፣ ስብሰባ፣ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ልማት ድጋፍ፣ ለህልውና ትግሉ ድጋፍ በመሳሰሉት ላይ አባላት እና ደጋፊዎች ይሳተፋሉ።ነገር ግን የደጋፊዎች ተሳትፎ ማኅበሩን የሚጠቅም ወይም የሚጎዳ ልዩ ሁኔታዎች ካሉ (ከውሳኔ አጀንዳዎች ውጭ ባሉ ጉዳዮች) በአስፈፃሚው ውሳኔ ይተገበራል።

2.2.5 ማንኛዉም አባል በማኅበሩ ደንብ መሰረት የሚሰጠዉን ማነኛውም አገልግሎት የማግኘት መብቱ የተጠበቀ ይሆናል፡፡ ማሕበሩ ለአባላት የሚሰጠው አገልግሎት፣ የድጋፍ ደብዳቤ፣ የምክር አገልግሎት፣ የምስክር ወረቀት፣ የጠበቃ ድጋፍ እና የመሳሰሉትን ማግኘት ሊሆን ይችላል።

## 2.3 አባልነት እና ደጋፊነት ግዴታ

2.3.1 የአማራ ማሕበር በኔዘርላንድ አባል ለመሆን አመልካቹ ደንቡን ለማሟላቱ የአባልነት ቅፅ ከመሙላቱ በፊት በሕገደንቡ መሰረት አባል መሆን ይችላል ወይስ አይችልም የሚለውን ውሳኔ ለመስጠት የሚያግዙ ቅድመ መጠይቆችን ሊሞላ እና ውሳኔ ሊሰጠው ይገባል። ይህ አካሄድ ለማኅበሩም ሆነ ለአባሉ ደህንነት አስፈላጊ በመሆኑ በትኩረት ይሰራል። ይህ አሰራር ደጋፊንም ይመለከታል።

2.3.2 የአማራ ማሕበር በኔዘርላንድ አባል ለመሆን የሚፈልግ ግለሰብ በማኅበሩ የተዘጋጀዉን የአባልነት ቅጽ መሙላት አለበት። የማኅበሩ ደጋፊ ለመሆን የደጋፊነት ቅፅ መሙላት አለበት።

2.3.3 ማንኛዉም አባል በደንቡ መሠረት የተወሰነዉን የአባልነት መዋጮ ያለማቋረጥ መክፈል ይጠበቅበታል።

2.3.4 የማሕበሩን መርህ፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ ውሳኔዎችና መመሪያዎች ተቀብሎ ሥራ ላይ ማዋል ይጠበቅበታል።

2.3.5 የብዙሃኑን ውሳኔዎች የመቀበልና የማክበር፣ የማሕበሩን የሥነ-ሥርዓት (ዲሲፕሊን) ሕግ ማክበር፣ ምስጢር መጠበቅ ግዴታ አለበት።

2.3.6 የማሕበሩን ዓላማና መርህ በተመቻቹ መድረኮች ሁሉ ማስተዋወቅ፣ እንዲሁም አባላትንና ደጋፊዎች ማሰባሰብ ይኖርበታል።

2.3.7 ማህበሩ የሚጠይቀዉን ማንኛዉም አግባብ ያለዉ ድጋፍና ዕርዳታ መስጠት አለበት።

2.3.8 የአባላት ወርሃዊና የመመዝገቢያ ክፍያን በባንክ ወይም በካሽ ለማኅበሩ ይከፍላሉ።

2.3.9 አንድ አባል ቢታሰር፣ ቢታመም ወይም ችግር ቢደርስበት የቤተሰቡ አባላት ወይም ወዳጅ ወይም ጉዳዩን በቅርበት የሚያውቅ ሌላ ማኅበርተኛ ለማኅበሩ አመራር በሠዓቱ የማሳወቅ ግዴታ አለበት። ማኅበሩ የእያንዳንዱን አባል እና ደጋፊ የአዳጋ ጊዜ የቅርብ ተጠሪ ይይዛል።

2.3.10 አንድ አዲስ አባል ወርሃዊ መዋጮ መክፈል የሚጀምረው ከተመዘገበበት ወር ጀምሮ ይሆናል። ልዩ ሁኔታዎች ካሉ አስፈፃሚው ውሳኔ ይሰራል።

2.3.11 አንድ አባል ከማኅበሩ በውሰት የወሰደውን ንብረት ቢጎድልበት፣ ቢጠፋበት፣ ቢበላሽበት መልሶ የመተካት ግዴታ አለበት። ማነኛውም አባል ወይም ደጋፊ በማኅበሩ የስራ ክፍሎች ተግባራት የመሳተፍ ግዴታ አለበት።

2.3.12 ማንኛውም አባል ለማኅበሩ የስራ ክፍል ተግባራት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚሰጠውን የሥራ ድርሻ ወይም በፍላጎቱ ተሳትፎ ማድረግ ይኖርበታል።

2.3.13 አንድ ግለሰብ በአባልነት ለመመዝገቢያ እና የአባላት ወርሃዊ መዋጮ በምክርቤቱ ወይም ጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ መሰረት የመክፈል ግዴታ አለበት። ልዩ ሁኔታዎች ካጋጠሙ የአስፈፃሚው ውሳኔ ይገበራል።

## 2.4 ከአባልነት ስለማስወገድ

2.4.1 አንድ አባል ያለ በቂ ምክንያት ለሶስት ተከታታይ ወራት የአባልነት መዋጮዉን ያልከፈለ አባል ከአባልነት ይሰረዛል።

2.4.2 አንድ አባል በፍላጎት ከአባልነት ለመልቀቅ በቃል ወይም በጽሑፍ ጥያቄ ሲያቀርብ መልቀቂያ ይሰጠዋል።

2.4.3 አንድ አባል ከማኅበሩ መሠረታዊ ዓላማዎች በተጻራሪ ከተንቀሳቀሰ ወይም የሌላ ተጻራሪ ድርጅት አባል ሆኖ ከተገኘ ከአባልነት ይሰረዛል።

2.4.4 አንድ አባል የማሕበሩን ምስጢር ማባከኑ ሲረጋገጥ በሥራ አስፈጻሚዉ ውሳኔ ከአባልነት ይሰረዛል።

2.4.5 የአባልነትም ሆነ ደጋፊነት መስፈርት ሳያሟላ ምክንያቱ ምንም ይሁን ሆኖ የተገኘ ያላሟላበትን ተነግሮት ከመዝገብ ይሰረዛል። ቅሬታዎች ካሉ የጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ ይፈፀማል።

2.4.6 የአማራ ሕዝብ እና የሌላ ማነኛውም አካል ልዩልዩ ጉዳዮች ቢያጋጥሙት ቅድሚያ የአማራን ሕዝብ መቀበል ወይም ማስቀደም ይኖርበታል። ከዚህ የተፃረረ እና እንደ አስፈላጊነቱ ቢያንስ አንዴ ተመክሮ ያላስተካከለ ከአባልነት መዝገብ ይሰረዛል።

2.4.7 ከማኅበሩ የወጣ ወይም የታገደ አባል ቀደም ብሎ ያዋጣውን ልዩ መዋጮም ሆነ የአባልነት ወርሃዊ ክፍያ አይመለስለትም።

2.4.8 አባሉ በስነምግባር እና ህግ ኮሚቴ ከአባልነት እንዲታገድ ሲወሰን እና ዉሳኔዉ ሰራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተቀባይነት ካገኘ ከአባልነት ይሰናበታል።

2.4.9 የአባልነትም ሆነ ደጋፊነት መስፈርት ሳያሟላ ምክንያቱ ምንም ይሁን ሆኖ የተገኘ ያላሟላበትን ተነግሮት ከመዝገብ ይሰረዛል ቅሬታዎች ካሉ የምክርቤቱ እና /ወይም የጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ ይፈፀማል።

2.4.10 የማኅበሩ አመራር፣ አባላት እና ደጋፊ በግል የፖለቲካ እና የ እምነት ድርጅት አባል ወይም ደጋፊ መሆን እንደተጠበቀ ሆኖ የማኅበሩን አመራር ፣አባላት እና ደጋፊ ልዩነት በሚያከብር አስተያየቶች እና ውሳኔዎች ሊሰጥ እና ሊቀበል ያልፈለገ ወይም ያልቻለ ከመዝገብ ይሰረዛል ።


2.4.11 ከማሕበሩ የተሰናበተ ግለሰብ እንደገና እንደ አዲስ አባል ለመሆን ከጠየቀ ጉዳዩ ለ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ቀርቦ 2/3ኛ ድምጽ ካገኘ አባልነት የሚፈቀድለት ይሆናል።

## 2.5 አባልነት የማይተላለፍ ስለመሆኑ

2.5.1 የማሕበሩ አባልነት ወደ ሌላ ወገን አይተላለፍም።

# 3 አንቀጽ 3 ፥ አስተዳደራዊ መዋቅር

## 3.1 የድርጅቱ አደረጃጀት



# 4 ጠቅላላ ጉባዔ ተግባርና ኃላፊነት

4.1.1 ጠቅላላ ጉባዔው አባላት በሙሉ የሚሳተፉበት የማሕበሩን አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴን በበላይነት ለመምራት የተሰየመ የሥልጣን አካል ነው።

4.1.2 ጠቅላላ ጉባዔው በየስድስት ወሩ ስብሰባዉን ያካሂዳል። አስቸኳይ ጉዳዮች ባጋጠሙ ወቅት እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። እንዲሁም በአባላት ሁለት ሶስተኛ ድምፅ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲጠራ ከተጠየቁና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል።

4.1.3 የአመራር ክፍሉ ሰብሳቢ፤ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሃፊ የጠቅላላ ጉባዔዉ ሰብሳቢ፤ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሃፊ ይሆናሉ። የአመራር ክፍሉ በተለያየ ምክንያት ሀላፊነት ካልተወጣ አስፈፃሚው ጠቅላላ ጉባዔውን ሊጠራም ሊመራም ይችላል።

4.1.4 ጠቅላላ ጉባዔው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን፤ የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴውን እና የስነምግባርና ሕግ ኮሚቴን ሪፓርት ያዳምጣል፤ ይመረምራል፤ ያጸድቃል፤ ይሽራል።

4.1.5 ጠቅላላ ጉባዔው በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ የተላለፉ ዉሳኔዎችንና መምሪዎችን የመመርመርና የማጽደቅ ሥልጣን አለዉ፡

4.1.6 በጠቅላላ ጉባዔው ከግማሽ በላይ (ሃምሳ አንድ ፐርሰንት) አባላት የተገኙበት ስብሰባ ምልዓት ጉባዔ ይሆናል፡፡

4.1.7 የጠቅላላ ጉባዔው ማንኛዉም ዉሳኔ በድምጽ ብልጫ ወይም በጋራ ስምምነት ይተላለፋል፡፡

4.1.8 ጠቅላላ ጉባዔው የመተዳደሪያ ደንቡን የማጽደቅ፣ የማሻሻልና የመለወጥ ሥልጣን አለዉ፡፡

4.1.9 ጠቅላላ ጉባዔው ሶስት አባላትን ከጠቅላላ ጉባዔው አባላት መካከል የምርጫ አስተባባሪ ኮሚቴ አድርጎ እየሠየመ በየሁለት ዓመቱ የአመራር አባላትን ምርጫ ያካሂዳል፤ ከሶስቱ አስመራጮች አንዱ ከስራ አስፈፃሚዎች መካከል፣ ቀሪ ሁለቱ ከአባላት የሚመረጡ ይሆናሉ። የአስመራጭ ተወካዮች ቅድሚያ ከአማራው ነገድ ይሆናሉ።

4.1.10 ጠቅላላ ጉባዔው የአመራር አባላትን በአመራረጥ ሕግናስርዓት መመረጣቸውን እና የተመረጡትን ግለሰቦች ፍላጎት አድምጦ ከተወያየ በኋላ በአብላጫ ድምፅ ያፀድቃል። ከተመረጡትም የአመራር አባላት መካከል ሊቀመንበሩ፤ ምክትል ሊቀመንበሩ እና ጸሐፊው ብቻ በጠቅላላ ጉባዔው ይመረጣሉ። ሌሎች የስራ ክፍፍሎች በአመራር አባላት የውስጥ ስምምነት ወይም ምርጫ ይወሰናሉ ።

4.1.11 ጠቅላላ ጉባዔው ሶስት አባላት ያሉት የስነምግባርና ሕግ ክፍል ይሰይማል። የስነምግባርና ሕግ ክፍል ኃላፊ በመሆን በጠቅላላ ጉባዔው የሚሠየም ይሆናል። የስነምግባርና ሕግ ክፍል ከ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ ጋር በትብብር የሚሰራ ቢሆንም ገለልተኝነቱን ለመጠበቅ እንዲቻል ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባዔው ይሆናል፤

4.1.12 ከማኅበሩ አባላት መሐከል 2/3ኛው አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባዔ ወይም ምክርቤት ስብሰባ እንዲጠራለት በፊርማ ከጠየቀ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ወይም ምክርቤቱ ሊቀመንበር የመጥራት ግዴታ አለበት።

4.1.13 የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ፣ምክር ቤቱ ወይም ጉባዔው በስድስት ወር አንድ ጊዜ የሚካሄደውን ጠቅላላ ጉባዔ ካልጠራ፤ በ1/3ኛ የአባላት ድጋፍ ከአገኙ አማካሪ ሸምጋይ ቦርዱ ወይም ንኡሳን ኮሚቴዎች አጠቃላይ ጉባዔውን ሊጠሩ ይችላሉ።

# 5 የስራ አስፈጻሚ ኮሜቴ

## 5.1 የስራ አስፈጻሚ ኮሜቴ ተግባርና ኃላፊነት

5.1.1 የሥራ አስፈጻሚ ኮሜቴዉ ከ ዘጠኝ (9) እስከ አስራ ሶስት(13) አባላት ይኖሩታል።

5.1.2 የስራ አስፈፃሚ ኮምቴ አካላት በስራ አስፈፃሚው አቅራቢነት ወይም ከአባላት በቀጥታ የሚመረጡ ይሆናሉ። እንደ አስፈላጊነቱ በጠቅላላ ጉባዔው ማስተቸት እና ማፀደቅ ይቻላል።

5.1.3 የአባላትን ቁጥር እና የተግባራትን ብዛት መሰረት ተደርጎ በየመደቦች ለሚወከሉ ዋና ሰዎች አስፈፃሚው ኮምቴ ካመነበት ከአባላት መልምሎ በአጋዥነት መድቦ ለምክርቤቱ በደብዳቤ ወይም በስብስባ አሳውቆ ማሰራት ይችላል። በአስፈፃሚው ስብሰባዎች የመደቡ ዋና ሀላፊ ወይም የተወከለ ብቻ መሳተፍ እና መወሰን ይችላል። የማኅበሩ መዋቅሩ የተሟላ ቁመና እስኪኖረው ድረስ ገንዘብ ያዥ፣ ሂሳብ ኦፊሰር ፣ንብረት ኦፊሰር እና አስፈፃሚው ያመነበት ኦፊሰር መደብ እንዲሳተፍ ማድረግ ይቻላል። በውሳኔ ላይ ድምፅ የሚሰጡ ግን የክፍሉ ሀላፊ ወይም የተወከሉ ብቻ ናቸው።

5.1.4 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል። አስፈፃሚው ኮምቴ ውጤታማ ስራ ከሰራ እና ጠቅላላ ጉባኤው ካመነበት ለተጨማሪ አንድ አመት ምክርቤቱ ማራዘም ይችላል። የጊዜ ገደቡ ከተጠናቀቀ በኋላ አዲስ ለተመረጡት እስኪረካከቡ እና የማስጀመሪያ አቅም ግንባታ ልምድ እንዲለዋወጡ ተጨማሪ እስከ ሶስት ወር ጠቅላላ ጉባኤው መፍቀድ ይችላል፣ የአፈፃፀሙ ውጤታማ እንዲሆን ድጋፍ ክትትል ያደርጋል።

5.1.5 በልዩ ልዩ ምክንያት አባላት ቢጎድሉ ለጉባኤው አቅርቦ ከአባላት መካከል ምትክ እንዲመረጥ ወይም እንዲሟላ ያደርጋል።

5.1.6 የማኅበሩን የእለት ተለት የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል።

5.1.7 ሕገ ደንቡን በማይጥስ ማሕበሩን ለማስተዳደር የሚዘጋጁ ልዩልዩ መሪዎችና የሥራ ዕቅዶችን በመንደፍ በአብላጫ ድምፅ ያፀደቀውን ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ ያስተቻል ያጸድቃል።

5.1.8 በጠቅላላ ጉባዔዉ የተላለፉ ውሳኔዎች በሥራ ላይ ያዉላል፤ በበላይነት ይቆጣጠራል።

5.1.9 ለጠቅላላ ጉባዔው በየ 3 ወሩ ሪፓርት ያሳውቃል፣ በየስድስት ወሩ ሪፖርት ያቀርባል ያስገመግማል።

5.1.10 ማኅበሩን በመወከል ከሌሎች ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ማሕበራት ወይም ሌሎች አካላት ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

5.1.11 መደበኛ ስብሰባዉን በየሳምንቱ ወይም በየሁለት ሳምንቱ ያደርጋል። አስፈፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ አስቸኳይ ስብሰባ መጥራት ይችላል።

5.1.12 ከግማሽ በላይ አባላት ጥያቄ ካቀረቡ ወይም አስቸኳይ ሁኔታ ከተፈጠረ ለ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አቅርቦ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲጠራ ይጠይቃል።

5.1.13 የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ውሳኔ በሚሹ ጉዳዮች ውሳኔ የሚሰጠው ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ በሚገኙበት ጊዜ ይሆናል።

5.1.14 የኮሚቴው ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ይተላለፋሉ፡፡ ሰብሳቢው ድምጽ የማይሰጥ ሲሆን የኮሚቴው ድምጽ እኩል በሚሆንበት ጊዜ የሰብሳቢው ድምጽ ወሳኝ ይሆናል፡፡

5.1.15 በአማራው ሕዝብ ላይ የተፈፀመውን መንግስት መር የዘር ማፅዳት እና ጄኖሳይድ ከፍተኛ ወንጀል የፈፀሙትን ኃይሎች ለፍርድ ለማቅረብ እንዲሁም ለማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት ድጋፍ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ዓለም አቀፍ የፍትህ እና ልማታዊ ተቋማት ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

5.1.16 የድርጅቱን የስድስት ወር የዕቅድ እና የስራ አፈፃፀም ሪፖርት መርምሮ በማፅደቅ ለጠቅላላ ጉባዔዉ ያቀርባል።

**5.1.17 የሊቀመንበሩ ተግባርና ኃላፊነት**

5.1.17.1 የሥራ አስፈጻሚዉን በሊቀመንበርነት ይጠራል ይመራል።

5.1.17.2 የማሕበሩን የሥራ እንቅስቃሴ በሃላፊነት ያስተባብራል።

5.1.17.3 ከስራ አስኪይጅ ኮሚቴ ጋር በመሆን ጠቅላላ ጉባዔውን ይጠራል ።

5.1.17.4 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በሚወስነዉ መሠረት ማኅበሩን ወክሎ ይደራደራል፤ ስምምነት ይፈራረማል።

5.1.17.5 ከጸሐፊውና ከገንዘብ ያዥ ጋር በመሆን የድርጅቱን የባንክ ሂሳብ ያንቀሳቅሳል።

5.1.17.6 የተለያዩ ንኡስ ኮሚቴዎች ሃላፊነታቸዉን መወጣታቸዉን ይቆጣጠራል፤ መመሪያ ይሰጣል።

### 5.1.18 የምክትል ሊቀመንበር ተግባርና ኃላፊነት

5.1.18.1 ሊቀመንበሩ በሌለ ጊዜ ተክቶ ይሰራል።

5.1.18.2 በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ የሚሰጡትን ሊሎች ተግባራት ያከናዉናል።

5.1.18.3 ለማኅበሩን እና የአስፈፃሚ አባል የስራ ክፍሎች ከሌሎች ሀገራት አቻ አማራ ማህበራት ጋር የትውቅ ስርዓት ያዘጋጃል፣ የስራ ልምድ እና መረጃዎች የሚለዋወጡበትን ስርዓት ይፈጥራል፣ ይደግፋል።

5.1.18.4 በማኅበሩ አፈፃፀም እና አባላት ዙሪያ ጥናት በማድረግ አወንታዊ ግብረመልስ ይሰጣል።

### 5.1.19 የዋና ጸሐፊ ተግባርና ኃላፊነት

5.1.19.1 የሥራ አስፈጻሚ፤ የጠቅላላ ጉባዔዉን ስብሰባዎች ቃል ጉባዔ ይይዛል።

5.1.19.2 የማሕበሩን የሥራ ዶኮሜንቶች ይይዛል፤ ይጠብቃል።

5.1.19.3 ከሊቀመንበሩ ወይም ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ ጋር በመመካከር የስብስባ አጀንዳዎችን ያዘጋጃል።

5.1.19.4 የማሕበሩ ከሌሎች አካላት ጋር የሚያደርገዉን የጽሑፍ ልዉዉጥ (ኮረስፓንደንስ) ያከናዉናል።

5.1.19.5 ከገንዘብ ያዡና ሊቀመንበሩ ጋር በመሆን የማኅበሩን የባንክ ሂሳብ ያንቀሳቅሳል።

5.1.19.6 ሰብሳቢው እና ምክትሉ በሌለበት ጊዜ ኮምቴ አባሉን ይሰበስባል። ነገር ግን የተሻለ መምራት የሚችል አለ ተብሎ በኮምቴው አባል ከታመነ ሰብሰቢው ወይም ምክትሉ ከኮምቴ አባላት መካከል ውክልና የሰጠው መምራት ይችላል።

## 5.2 የአደረጃጀት ክፍል ተግባርና ኃላፊነት

5.2.1 በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰየም የክፍል ኃላፊ ይኖረዋል። ኃላፊዉ ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ ዉስጥ ነው።

5.2.2 በተለያዩ ከተሞች ያሉ አማሮችን የአማራ ማኅበር አባል ወይም ደጋፊ አደረጃጀት እንዲገቡ ያስተባብራል ይሰራል።

5.2.3 የአባላት ስነ ምግባር ደንቦችንና የቁጥጥር መመሪያዎችን ያዘጋጃል። ነባርም ሆነ አዲስ አባላት እና ደጋፊዎችን በተናጠል ፡ የመገናኛ፣ ልዩልዩ የመልክት መለዋወጫ ግሩፖችን ይፈጥራል፣ ይቆጣጠራል።

5.2.4 ማኅበሩን ለማጠናከር የአባልነት እና ደጋፊ መመልመያ እና መሙያ መስፈርቶችን፣ ቅፆችን በማዘጋጀት ለሚመለከተው ያሳውቃል ይደግፋል።

5.2.5 አባላት የሚጠበቅባቸዉን ግዴታዎች እየተወጡ መሆናቸዉን ይከታተላል።

5.2.6 የማኅበሩን ግብና ተልዕኮ መሰረት በማድረግ ለአባላት የአቅም ግንባታ ስልጠና (የግንዛቤ ማስጨበጫ ሴሚናር ሲምፖዚየም እና ስልጠናዎች) ያዘጋጃል፤ ይሰጣል።

5.2.7 መደበኛ አባላት ለማኅበሩ እና ለአማራ ማድረግ የሚገባቸውን ለማድረጋቸው እራሳቸውን የሚገመግሙበት መጠይቆች ወይም መድረኮችን ያዘጋጃል።

5.2.8 የማኅበሩን የአሰራር መርህና ስልት ለሚመለከታቸዉ አካላት በስፋት ከሕዝብ ግኑኙነት ጋር በመደጋገፍ ያሰራጫል፤ ተቀባይነት ኢንዲያገኝ ይሰራል።

5.2.9 ማኅበሩን ውጤታማ የሚያደርጉ አደረጃጀት መነሻ ሀሳብ በማዘጋጀት ለአስፈፃሚ ያቀርባል። ሲታመንበት በምክርቤቱ ፀድቆ ተግባራዊ ይሆናል።

5.2.10 ስላከናወናቸው ተግባራት አስፈፃሚ ኮሚቴዉ ሪፖርት ያቀርባል።

## 5.3 የፋይናንስና የንብረት አስተዳደር ክፍል ተግባርና ኃላፊነት

5.3.1.1 በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰየም የክፍል ኃላፊ ይኖረዋል። ኃላፊዉ ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ ዉስጥ ነው።

5.3.1.2 የገቢና ወጪ መዝገብ አዘጋጅቶ የማኅበሩን ገቢና ወጪ እንቅስቃሴ ይመዘግባል ወይም መመዝገቡን ያረጋግጣል፡፡

5.3.1.3 በሊቀመንበሩ ሲፈቀድና ደንቡን የተከተለ መሆኑን በቅድሚያ ሲያረጋግጥ እነዲሁም በማስረጃ የተደገፈ ሆኖ ሲገኝ ክፍያዎችን ያዘጋጃል፣ የክፍያ ትዕዛዞችን ይፈርማል፡፡

5.3.1.4 የማኅበሩን ቋሚና አላቂ፣ ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ይመዘግባል፤ ለተገቢው አገልግሎት መዋላቸውን ይከታተላል፡፡

5.3.1.5 ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር በመተባበር የማኅበሩን ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፤ ለውሣኔ ለሚመለከተው ክፍል ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፡፡

5.3.1.6 የኮሚቴው እና ጠቅላላ ጉባዔ ስራማስኬጃ በጀት ፣ የገንዘብ አጠቃቀምና አያያዝ መመሪያ ያወጣል፤ አመራሩ አምኖበት ምክርቤቱ ወይም ጉባዔው ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

5.3.1.7 አስፈፃሚው፣ የአስፈፃሚው ሊቀመንበር ውሳኔ የሚንቀሳቀስ በጀት ወይም ገንዘብን ውሳኔ መነሻ ለምክርቤት ወይም ጉባዔው በአስፈፃሚው ቀርቦ ሲፀድቅ ተግባራዊ ይሆናል፡፡ እስኪፀድቅ ድረስ በአስፈፃሚው ኮምቴ አብላጫ ድምፅ ውሳኔ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

#### 5.3.2 የገንዘብ ያዥ ተግባርና ኃላፊነት

5.3.2.1 በደንቡ መሠረት የማኅበሩን ወጪና ገቢ ሰነዶችን ከሒሳብ ሹሙ ጋር በመተባበር ይይዛል፡፡

5.3.2.2 ከአባላትና ከሌሎች የገቢ ምንጮች የሚሰበሰብ ገንዘብ በማኅበሩ የባንክ ሂሳብ ገቢ ያደርጋል፡፡

5.3.2.3 ከስራ አስፈፃሚው ሊቀመንበር እና ከጸሐፊዉ ጋር በመሆን የድርጅቱን የባንክ ሂሳብ ያንቀሳቅሳል፡፡

5.3.2.4 የማኅበሩን ሂሳብ ከሂሳብ ሹሙ ጋር በመሆን በቁጥጥር ኮሚቴው ያሰመረምራል፡፡

#### 5.3.3 የሒሳብ ሹም ተግባርና ኃላፊነት

5.3.3.1 ከገንዘብ ያዥዉ ጋር በመሆን የድርጅቱን ገንዘብና ወጪና ገቢ ይመዘግባል፡፡ የማኅበሩን የገቢና ወጪ ሰነዶች ይይዛል፡፡

5.3.3.2 ሂሳቡን ከገንዘብ ያዡ ጋር በመሆን ኦዲት ያስደርጋል፡፡

5.3.3.3 ማንኛውንም የገቢና የውጪ ደረሰኝ ሰነዶች ትክክለኛነት ያረጋግጣል፡፡ ይቆጣጠራል፡፡

5.3.3.4 የማኅበሩን ገንዘብ ለምን ተግባር እንደዋለ እና ከምን ደረጃ ላይ እንዳለ የሂሣብ ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል፡፡

5.3.3.5 የአባልነት መመዝገቢያና በየወሩ አባላት ወርሃዊ የአባነት ክፍያ በሰዐቱ መከፈሉን ይከታተላል፡፡ ይመዘግባል፡፡ የገቢና የወጪ ደረሰኞችን ያዘጋጃል፡፡

5.3.3.6 የማሕበሩን የወርሃዊ መዋጮ ግዴታቸውን ያልተወጡ አባላትን የስም ዝርዝር ነቅሶ በማውጣት ሪፖርትን ለመሪው ወይም ለሚመለከተው ለሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ያቀርባል፡፡

5.3.3.7 የሰው ኃይል መጠኑ እንደ ተግባሩ እና አባሉ ብዛት በአስፈፃሚው ተወስኖ ምክርቤቱ ወይም ጠቅላላ ጉባዔው ሲያፀድቅ ከአንድ ባላይ ማድረግ ይቻላል፡፡

5.3.3.8 በጠቅላላ ጉባኤው ሲጠየቅ የማህብሩ ሂሳብ በገለልተኛ አካል እንዲጣራ ያስተባብራል፡፡

### 5.4 የታዳጊ ህፃናትና የወጣቶች ክፍል

5.4.1 በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰየም የክፍል ኃላፊ ይኖረዋል፡፡ ኃላፊዉ ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ ዉስጥ ነው፡፡

5.4.2 የታዳጊ ሕፃናትና የወጣቶች ኮሚቴ ሶስት አስተባባሪ አባላት ይኖሩታል፡፡

5.4.3 ከማኅበሩ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ጋር በመተባበር እና በመመካከር ይሠራል፡፡

5.4.4 ሆላንድ ውስጥ ለተወልዱ ልጆች የአገራቸውን ታሪክና ብሎም በአማራው ስነልቦና፣ ባህልና ወግ ታንፀው እንዲያድጉ ለማድረግ ወላጆችን ያበረታታል። ወላጆች በዚህ መስክ ያላቸውን ልምድ እንዲለዋወጡ ለማድረግ የምክክር መድረክ በየጊዜው በማዘጋጀት ሁኔታዎችን በትጋት ያመቻቻል።

5.4.5 ወጣቶች እርስ በርሳቸው እንዲተዋወቁና ብሎም በሂደት የራሳቸውን የወጣቶች ማዕከል እንዲፈጥሩ ለማስቻል ለውጣቱ የሚሆኑ የተለያዩ ዝግጅቶችን ከውላጆቻቸው ጋር በመመካከር እንደ አመቺነቱ እና እንደሁኔታው በየጊዜው ያዘጋጃል። ያበረታታል።

5.4.6 የታዳጊ ሕፃናት ወላጆችና በተለይም የወጣቶቹን ተሳትፎና ፍላጎትን ለማሳደግ በየጊዜው የሥራ እቅዶችን ከማኅበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ጋር በመመካከርና በመተባበር እቅድ ያውጣል። ያስፈጽማል።

5.4.7 የሥራ አፍፃፀም ዘገባዎችን እና በሂደት ያጋጠሙ ችግሮችን በየጊዜው ለሥራ አመራር ኮሚቴው ሪፖርት ያቀርባል።

## 5.5 የሕዝብ ግንኙነት እና ዲፕሎማሲ ክፍል ተግባርና ኃላፊነት

5.5.1 በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰየም የክፍል ኃላፊ ይኖረዋል። ኃላፊዉ ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ ዉስጥ ነው።

5.5.2 የማኅበሩን ዓላማና ማናቸውም እንቅስቃሴ፤ የዜና ማሰራጫ አውታሮችን በመጠቀም በሕዝብ ዘንድ እንዲዳረስና እንዲሰርጽ ያደርጋል፤ የማኅበሩን ገጽታ ይገነባል፣ ያስተዋውቃል። የማኅበሩን ሚዲያወች ይከፍታል ወይም ያስከፍታል።

5.5.3 የማኅበሩን ተልዕኮዎችና ዓላማዎች መሠረት ያደረጉ ዜናዎች፣ መረጃወች፣ ቃለ መጠይቆች፣ ስብሰባወች፣ ዉይይቶችና ሌሎች ተመሳሳይ መልዕክቶች የሚተላለፉበትን ዘዴ ይቀይሳል፤ ያሠራጫል፤ ተፈፃሚነቱን ይከታተላል።

5.5.4 የማስታወቂያ፡ የቅስቀሳ፤ ሕዝብን ማንቃት እና ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎችን ያቅዳል፣ ዕቅዱ በአመራር ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል።

5.5.5 የእለት ከእለት ስራዎችን እየተከታተለ የማኅበሩን ሕገደንብ በጠበቀ ቢያንስ በማኅበሩ ሰብሳቢ እና የሚመለከተው አካል ቅድሚያ አስተያየት በመቀበል ሲያምንበት ለብዙሀን መገናኛዎች፣ ለዐማራ ሕዝብና ለሚመለከተው ሁሉ መረጃዎችን በማኅበሩም ሆነ በሌላ ሚዲያ ያሰራጫል። በአጠቃላይ የማኅበሩን የቃለ አቀባይ ሚና ይጫወታል።

5.5.6 የአማራው ሕዝብ የማኅበሩን አላማ ተረድቶ በዙሪያው እንዲሰባሰብ የሚያስችል የቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ ሥራ ይሠራል።

5.5.7 በአማራ ሕዝብ ላይ የሚፈጸመውን የዘር ማጥፋት ዘመቻ፣ ግፍና በደል፣ ስለዐማራ ሕዝብ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ እንቅስቃሴዎች እና ሁኔታዎች እየተከታተለ መረጃዎችን በማጠናቀርና በማደራጀት በመገናኛ ብዙሃን በሚመጥን ደረጃ መረጃዎችን፤ መግለጫዎችን፤ ማብራሪያዎችን ወዘተ ያዘጋጃል፤ ያቀርባል፤ ያሰራጫል፤ ሰንዶ ያስቀምጣል።

5.5.8 የተለያዩ ሕዝባዊ ሰልፎችንና የሻማ ማብራት ፕሮግራሞችን ያስተባብራል። ለሕዝባዊ ሰልፍች የሚሆኑ መፈክሮችን፤ በራሪ ወረቅቶችን ያዘጋጃል።

5.5.9 በዚህ ኢሰብአዊ ድርጊት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተሳተፍ አካላት በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት እንዲጠየቁ ከሚመለከታቸው የፍትህና የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ጋር በመተባበር ሊሰራ ይችላል።

5.5.10 በተመረጡ ከተሞች ቢያንስ በየ ዓመቱ አባላቱ የሚተዋወቅበትን የሚዝናናበትን፣ የዐማራውን ሁለንተናዊ ገጽታ የሚያመላክቱ ስብሰባዎች ፣ ፌስቲቫሎችና ሲምፖዚየሞች ያዘጋጃል።

## 5.6 የዕቅድዝግጅት፣ጥናትና ምርምር ክፍል ተግባርና ኃላፊነት

5.6.1 በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰየም የክፍል ኃላፊ ይኖረዋል። ኃላፊዉ ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ ዉስጥ ነው።

5.6.2 በአማራዉ ሕዝብ አሰፋፈርና ብዛት፤ በታሪኩ፣ በኢኮኖሚው፣ በባህላዊ፣ በማህበራዊና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ልዩ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፤ እንዲሁም የአማራውን ሕዝብ የወደፊት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ይነድፋል::

5.6.3 ለአባላት ትምህርትና ሥልጠና ይሰጣል። እዚህ በውጭ የተወለዱ ልጆች ወጣቶች ታሪካቸውን፣ ባህላቸውንና ቋንቋቸውን እንዲያውቁ ያስተምራል።

5.6.4 የማኅበሩን የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅድ፣ ስልትና ስትራቴጂ ያዘጋጃል። ለስራ አስፈጻሚና ለምክር ቤቱ አቅርቦ ያጸድቃል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል።

5.6.5 የድርጅቱ አባላት በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያስችል የተለያየ የሥልጠናና የአቅም ግንባታ ስልቶችን ይቀይሳል፣ በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሲፈቀድም ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል።

5.6.6 በድርጅቱ እንቅስቃሴ ውጤት ላይ አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያርጉ የሚችሉ ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎችን በመከታተል በመለየት የሚያበረታታ ወይም ከአሉታዊ ጉዞው የሚወጣበትን የመፍትሄ ጥናት በማድረግ ለሚመለከተው በወቅቱ ያቀርባል ይመክራል።

5.6.7 የተለያዩ አለማቀፋዊ፣ አካባቢያዊና አገራዊ ሁኔታዎችን፣ የኃይል አሰላለፎችን በመገምገም በዐማራ ሕዝብ እና በድርጅቱ እንቅስቃሴ የሚያመጣውን ውጤት ይገመግማል፤ አቅጣጫ ያስቀምጣል።

5.6.8 ስላከናወናቸው ተግባራት አስፈፃሚ ኮሚቴዉ ሪፖርት ያቀርባል።

## 5.7 የገቢ ማመንጫና የሰብዓዊ ድጋፍ ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት

5.7.1 በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰየም የክፍል ኃላፊ ይኖረዋል። ኃላፊዉ ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ ዉስጥ ነው።

5.7.2 ማኅበሩ ቋሚና አስተማማኝ የገቢ ምንጭ የሚያገኝበትን መንገድ ያጠናል፤ ዕቅዶችንና ፕሮጀክቶችን ያዘጋጃል፤ ስልትና ስትራቴጂ እየቀየሰና ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ ጋር በመመካከር የአተገባበር ስርዓት ይዘረጋል።

5.7.3 የዐማራ ሕዝብ በየኢኮኖሚ አቅሙ የሚጎለብትበትን የአጭርና የረዥም ጊዜ የኢኮኖሚና ኢንቨስትመንት ፖሊሲዎችን ያጠናል፣ዕቅዶችንና ፕሮጀክቶችን ያዘጋጃል፣ ወደ ተግባር እንዲቀየሩ በአስፈፃሚው በኩል በምክር ቤት ያስፀድቃል፤ ተፈፃሚነቱንም ይከታተላል።

5.7.4 የዐማራ ማህበራት በየአካባቢያቸው የገቢ ማመንጫ፣ አቅም የሌላቸውን መርጃ እና ኢኮኖሚያዊ ትስስር የሚፈጥሩ የንግድ ስራዎችን እንዲያቋቁሙ ድጋፍ ያደርጋል።

5.7.5 የዲያስፖራው እና አገር ቤት ያለው የዐማራ ሕዝብ በንግድ፣ በኢንቨስትመንት እና በውጭ ምንዛሬ ልውውጥ ትስስር እንዲፈጥር የተለያዩ ስትራቴጂዎችን ቀርፆ ተግባራዊ እንዲሆን በአስፈፃሚው ገምግሞ ለምክር ቤቱ ቀርቦ እንዲፀድቅል ያስደርጋል ያስተገብራል።

5.7.6 ከለጋሽ ድርጅቶችና መንግሥታት ድጋፍ ያሰባስባል።

5.7.7 ከተለያዩ የእርዳታና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር ግንኙነቶችን በማድረግ የሰብዓዊ እርዳታ ያሰባስባል።

5.7.8 በሰው ሰራሽም ሆነ በተፈጥሯዊ መንገድ በህይወታቸው፣ በአካላቸው፣ በንብረታቸው ጉዳት የደረሰባቸውን፣ የተፈናቀሉ፣ የተሰደዱና ተመሳሳይ ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖቻችንን ለመደገፍ ከዓለም ዓቀፍ ማህበረሰብ፣ በጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ መንግሥታት እና ከመላው ዐማራ በዓይነትና በገንዘብ ርዳታ ለማሰባሰብ ስልቶችን ቀይሶ ይሰራል።

5.7.9 ድጋፉ ለታለመለት አላማ መድረሱን ሊያስረዱ የሚያስችሉ ማስረጃዎችን ይሰበስባል፤ ይይዛል።

## 5.8 የመረጃና ቴክኖሎጅ ክፍል ተግባርና ኃላፊነት

5.8.1 በምክር ቤት የሚሰየም የክፍል ኃላፊ ይኖረዋል። ኃላፊዉ ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ ዉስጥ ሊሆን ይችላል።

5.8.2 የማኅበሩን ፌስቡክ፣ ድረገፅ፣ ዮቲዩብ፣ ትዊተር፤ የአባላት መገናኛ ፕላትፎርሞችና ሌሎች ተመሳሳይ የመገናኛና ማሰራጫ ዘዴዎች የሚቋቋሙበትን ስርዓት ይዘረጋል፤ ተፈፃሚነቱንም ይከታተላል፤ ማንኛውንም የገቢና የውጪ ደረሰኝ ሰነዶች ትክክለኛነት ያረጋግጣል። ይቆጣጠራል።

5.8.3 የማሕበሩን የመተዳዳሪያ ደንብ ማህበረሰቡ እንዲያውቁ ያደርጋል ።

5.8.4 አጠቃላይ የማኅበሩን መረጃዎች ያደራጃል፤ በዳታ ቤዝ ያስቀምጣል፤ በሚፈለግበት ጊዜ ጥቅም ላይ እንዲዉሉ ያደርጋል።

5.8.5 የማኅበሩን አባላት ወሳኝ መረጃዎች ያሰባስባል፤ በአማራዊ ማንነታቸው አጠራጣሪ ሁኖ የተገኘን እና ማኅበሩን ሊጎዳ የሚችልን በአግባቡ በማጥናት እና በመሰነድ ለአስፈፃሚው አቅርቦ በሥራ አስፈፃሚው አማካኝነት ተጣርቶ ዉሳኔ እንዲሰጥበት ይሰራል።

5.8.6 አዳዲስ አባላት ማኅበሩን ከመቀላቀላቸዉ በፊትም ሆነ የገቡትን መረጃ በማሰባሰብ ስለግለሰቦቹ ማንነት ከአደረጃጀት ክፍሉ ጋር የጋራ እቅድ አቅዶ ይሰራል።ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ መረጃዉን ያቀርባል።

## 5.9 የስደተኞች እንግዶች አቀባበል ድጋፍ ክትትል ክፍል

5.9.1 በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰየም የክፍል ኃላፊ ይኖረዋል። ኃላፊዉ ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ ዉስጥ ነው።

5.9.2 በተለያዩ መንገዶች ወደ ኔዘርላንድ የመጡ አማራዎችን በአካልም ይሁን በልዩልዩ መገናኛ ሚዲያዎች አስፈላጊ ምክር ድጋፍ ያደርጋል

5.9.3 የጥገኝነት ጥያቄ ተቀባይነት ያገኙም ሆነ ያላገኙ የማኅበሩ አባል ወይም ደጋፊ እንዲሆኑ ይሰራል።

5.9.4 አስፈላጊ መረጃውችን፣ ጠበቆችን ፣ፖለቲከኞችን የመሳሰሉትን በማማከር ግንዛቤ ተወስዶ ጥገኝነት በተገቢው እንዲያስረዱ መደገፍ ወይም ደጋፊዎችን ማመቻቸት ይሰራል።

5.9.5 በተለያዩ ስምሪቶች አማራውያን እንግዶች ለምሳሌ ስፖርተኞች፣ አርቲስቶች፣ ህዝባዊ ባለሀብቶች፣ ታዋቂዎች የመሳሰሉት ኔዘርላንድ ሲመጡ ወይም እንዲመጡ ሲደረግ በአማራዊ እሴት ፍቅር አቀባበል ፣ ድጋፍ ማድረግ ።

# 6 የስነምግባር እና ሕግ ክፍል

## 6.1 የስነምግባር እና ሕግ ክፍል ተግባርና ኃላፊነት

6.1.1 በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰየም የክፍል ኃላፊ ይኖረዋል። ኃላፊዉ ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ ዉስጥ ነው።

6.1.2 በአባላት መካከል አለመግባባት ቢኖር የማግባባት እና መፍትሄ የማፈላለግ ጥረት ያደርጋል።

6.1.3 በአባላት ቅሬታ ሲነሳ ደንቦችን እና መመሪያዎችን ተከትሎ የተሰሩ እንደሆነ አይቶ አስተያየት ምላሽ እና መፍትሄ ይሰጣል፤ ለምክርቤቱ ያሳውቃል።

6.1.4 በገንዘብ አያያዝ እና አጠቃቀም ሥርዓት፣ በመተዳደሪያ ደንብ አፈጻጸም፣ የአባልነት ጉዳዮች እና ሌሎች ድርጂታዊ ጉዳዮች ላይ የአሠራር እና የሕግ ክፍተቶች እንዳይኖሩ የሚያስችል ድርጂታዊ ብቃት እንዲኖር ይሰራል፤ የመፍትሄ ሃሳቦችን በማቅረብ እና የተሻሉ አሰራሮችን በማዘጋጀት የስራ ክፍል አመራሩን ያግዛል።

6.1.5 በየወቅቱ የሚሰሩ፣ በመተዳደሪያ ደንቡ የተቀመጡ እና የታቀዱ ተግባራትና ኃላፊነቶችን ይከታተላል፤ የተዛባ አሰራር እና ዲሞክራሲያዊ ያልሆነ አስተሳሰብ እንዲታረም በማድረግ እና ከብዙሃን ፈቃድ ውጭ የሆነ እና ስርዓት ከተዘረጋለት መንገድ ውጭ ወይም ውሳኔ አሰጣጥ ውጭ የሆነ አሰራር እንዳይኖር የሚያስችል ድርጂታዊ አሰራርን ያስተካክላል፤ ድርጅቱ በሚያደረጋቸው እንቅስቃሴዎች ሁሉ ህጋዊ ችግር ላይ የሚጥሉ እንዳይሆኑ ምክር እና ከለላ የሚያገኝበትን ሙያዊ የመከላከል እገዛ ያደርጋል።

6.1.6 በመገናኛ ብዙሃን፣ በማህበራዊ መገናኛዎች ወይም በድርጅቱ መረጃዎች ላይ የሚካተቱ ጉዳዮች ይዘት ህጋዊነትን የተከተለ መሆኑን ይከታተላል።

6.1.7 የድርጅቱ አደረጃጀት እና አሠራር ህጋዊነት ያለው እንዲሆን ምክር ይሰጣል፤ አቅጣጫ ይጠቁማል።

6.1.8 በሕግ ጉዳዮች ላይ ድርጅቱን ወክሎ ይቀርባል፤ የፍርድ ቤት ጉዳይ ቢኖር ንቅናቄዉን ወክሎ በጥብቅና የሚቆም ባለሙያ ይመድባል ወይም ይፈልጋል።

6.1.9 የድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብና የልዩ ልዩ ክፍሎችን የውስጥ መመሪያዎች በመጣስ የአሰራር ችግር በሚፈጥር ማንኛውም የድርጅቱ አባል ላይ የሥነ ሥርዓት እርምጃ እንዲወሰድ ሪፖርት ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ወይም /እና ለምክርቤቱ ያቀርባል።

6.1.10 በምክርቤቱ እና በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን አስተያየቶች ድጋፍ ጥያቄዎች መነሻ አድርጎ በእቅድ ያከናውናል።

6.1.11 በየወሩ ስለተከናወኑ ተግባራት ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፤ ለስራ ክፍሎች የድጋፍ ግብረመልስ ይሰጣል ፣ በአስፈፃሚው፣ ምክርቤቱ ስብሰባዎች በመሳተፍ ያስገነዝባል።

# 7 የአማካሪ እና ሽምጋይ ቦርድ ክፍል

## 7.1 የአማካሪ እና ሽምጋይ ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት

7.1.1 በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰየም የክፍል ኃላፊ ይኖረዋል። ኃላፊዉ ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ ዉስጥ ነው።

7.1.2 የአማካሪናሽምጋይ ቦርድ አባላት ቁጥር ከአምስት እስከ ሰባት ሲሆኑ በእውቀት የበሰሉ፣ በብዙሀኑ የሚታመኑ፣ ከተለያየ ጎሳ መዋለድም ሆነ ጋብቻ ነፃ መሆን አለባቸዉ። ከማነኛውም ሱስ ነፃ የሆኑ፣ የተለያየ አመለካከትን ሊያዳምጡ የሚችሉ ፣ ሚስጥር ጠባቂ እና ታጋሽ ሊሆኑ ይገባል።

7.1.3 ማኅበሩን አደጋ ላይ የሚጥሉ ልዩ ልዩ ችግሮች ሲፈጠሩ፣ ችግሮቹ ከመባባሳቸው በፊት የመፍትሔ እርምጃዎች በሚመለከተው እንዲወሰድ ሀሳብ ያቀርባሉ።

7.1.4 የአማካሪውናሽምጋይ ቦርድ አባላት በምክር ቤቱ መነሻ ተመርጦ ቀጥታ በጠቅላላ ጉባዔዉ የሚፀድቅ ይሆናል። ተጠሪነታቸውም ለጠቅላላ ጉባዔው ይሆናል።

7.1.5 የአማካሪውናሽምጋይ ቦርድ አባላት ያላቸውን ሰፊ ልምድ እና ሙያ ተጠቅመው እጅግ አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች አመራሩን እና የስራ ክፍሎችን ያማክራሉ፤

7.1.6 የአማካሪውናሽምጋይ ቦርድ አባላት የትግሉን ወሳኝ ጉዳዮች እየለዩ እና እያጠኑ አዳዲስ ሃሳቦችን እና ጥናቶችን ለአመራሩ ያቀርባሉ፤ ስልጠናዎችን ይሰጣሉ፤

7.1.7 የአማካሪውናሽምጋይ ቦርድ አባላት አመራሩ ለይቶ በሚጠይቃቸው ጉዳዮች ላይ ዝግጅት እና ጥናት አድርገው የተደራጇ ሃሳብ እና ምክር ይሰጣሉ፤

7.1.8 የአማካሪናሽምጋይ ቦርድ አባላት ከማኅበሩ አመራር አካላት አቅም በላይ የሆኑ የማሕበሩን ሕልውና የሚፈታተኑ ሆነው በተገኙ ችግሮች ላይ ያማክራሉ፣ ለችግሩ መፍትሔ ይጠቁማሉ።

7.1.9 የማሕበሩን የስራ እንቅስቃሴ ለማጠናከር ሲባል በየሁለት ወራት ከማኅበሩ አመራር እና ከምክርቤት አባላት በተናጠልም በሆነ በጋራ ስብሰባ በመቀመጥ ድክመቶቹን በጋራ በመገምገም አዳዲስ ስልቶችን የማማከር ሚና ይኖረዋል።

7.1.10 የማሕበሩ አመራር አባላት በማንኛውም ጊዜ የአማካሪ ቦርዱን ማግኘትና በሚደረጉ ስብሰባወች ላይ እንዲሳተፍ በተጠየቁ ጊዜ ይሳተፋሉ ሆኖም በውሳኔ ድምፅ አይሳተፉም።

7.1.11 በማኅበሩ ውስጥ የሚፈጠሩ ማናቸውም አለመግባባቶች እና ችግሮች በሕገደንቡ መሰረት ጉዳዮን መርምሮ አድምጦ ይሸመግላል መፍትሔ ይሰጣል፤ የደረሰበትን ውሳኔ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል። ምክርቤቱ ይወስናል። ይህም ሁኖ መፍትሄ ካልመጣ የአባላት ጉባዔው ውሳኔ ይተገበራል ።

7.1.12 የአገልግሎት ዘመኑ ሁለት አመት ሲሆን ምክርቤቱ ወይም ጉባዔው ሲያምንበት ሊያራዝምወይም ሊያሳጥር እና በአዲስ ሊመርጥ ይችላል።

# 8 ክፍል አራት: ልዮ ልዮ ድንጋጌዎች

## 8.1 አንቀጽ 35. የማኅበሩ የገቢ ምንጭ

8.1.1 የማኅበሩ ዋና የገቢ ምንጭ ከአባላት በሚሰበሰበዉ ወርሐዊ ክፍያ ይሆናል። ክፍያዉ በስምምነት ቀጥታ ከአካውንት ወይም በደረሰኝ ይሰበስባል።

8.1.2 ማኅበሩ የገቢ ምንጩን ለማዳበር በስሙ የሶሻል ክለብ ፣ እና ልዩልዩ ፕሮጀክት ሊያቋቁም ይችላል። ማኅበሩን በማይጎዳ ይልቁን ትርፍ ለሚያስገኙ የአባላት ፈጠራዎች አበርክቶቶች በግፅ ለሚታወቁ ወጭ ላስወጣቸው ማካካሻ ልዩልዩ ማበረታቻ ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል። የአሰራር ስርዓት በአስፈፃሚው መነሻ ቀርቦ ምክርቤቱ ሲያፀድቅ ይተገበራል።

8.1.3 የማኅበሩን ዓላማና ግብ ከሚደግፉ በጎ አድራጊ ግለሰቦችና ድርጅቶች የሚገኝ አበርክቶ (ግራንት) መቀበል ይችላል።

8.1.4 ማኅበሩ እንደ አሰፋላጊነቱ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞች እያዘጋጀ ገቢ ሊሰበስብ ይችላል።

8.1.5 የማኅበሩ ገንዘብ በራሱ ስም በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ተቀማጭ ይሆናል።

## 8.2 የገንዘብና ንብረት ባለቤትነት

8.2.1 ማሕበሩ በስሙ የተሰበሰበና የተቀመጠ ገንዘብና ንብረት የራሱ የአማራ ማሕበር ንብረት ነዉ።

8.2.2 የማሕበሩ ተልዕኮ ወይም ህልዉና ሲያከትም፤ በስሙ የተያዘዉ ገንዘብና ንብረት ምን ላይ መዋል እንዳለበት በጠቅላላ ጉባዔዉ ይወስናል።

## 8.3 መተዳደሪያ ደንቡን ስለማሻሻል

8.3.1 ከማሕበሩ ጠቅላላ አባላት ውስጥ ሁለት ሶስተኛው ሕገ ደንቡ እንዲሻሻል ከጠየቀ ሊሻሻል ይችላል።

8.3.2 ጥያቄዉ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ በኩል ለምክር ቤት ይቀርባል። ምክር ቤቱም ተወያይቶበት ለጠቅላላ ጉባዔዉ ያቀርባል።ጠቅላላ ጉባዔዉ ተወያይቶ በሚሰጠዉ ውሳኔ መሠረት ተግባራዊ ይሆናል።

## 8.4 ደንቡን ሥራ ላይ ስለማዋል

8.4.1 ይህ መተዳደሪያ ደንብ በአስፈፃሚው ለጠቅላላ ጉባዔው ቀርቦ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚነት ይኖረዋል። ጠቅላላ ጉባዔ ከመቅረቡ በፊት አስፈፃሚው የጋራ ማድረግ ይችላል።

8.4.2 ይህ መተዳደሪያ ደንብ በአስፈፃሚው ለጠቅላላ ጉባዔው ቀርቦ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚነት ይኖረዋል። ጠቅላላ ጉባዔ ከመቅረቡ በፊት አስፈፃሚው የጋራ ማድረግ ይችላል።

8.4.3 ይህ መተዳደሪያ ደንብ ጠቅላላ ጉባዔዉ ተወያይቶ ከዛሬ .............................. ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል አጽድቆታል።